# መግለጫ

(ት.ህ.ሓ.ኢ.ድ)

የትግራይ ህዝብ ነፃ ኣውጪ ድርጅት

የመጀመሪያ እትም

በየካቲት ወር 1968 ዓ/ም

## ማውጫ


መቅድም ............ v

መግቢያ ............ viii

I አሁን እስካለው ሁኔታ

1- ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ............ 1

ሀ. ፖለቲካዊ ስልጣን ............

ለ. የፖለቲካ ነፃነት አለመኖር ............ 5

ሐ. ብሄራዊ ተፅእኖ ............ 7

መ. ፕሮፓጋንዳ ............ 10

2- ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ............ 12

ሀ. የመሬት ይዞታው ስርዓትና ችግሩ ......

ለ. የኢንዱስትሪዎች አለመስፋፋት ............ 13

3- ማኅበረሰባዊ ሁኔታዎች ............ 14

ሀ. ራስን መጣል [ዲ-ሁማናይዜሽን] ...

ለ. የማኅበረሰቡ ወደ ኋላ መቅረትና እረፍት ማጣት 15

II መፍትሔው

ሀ. ብሔራዊ ትግል ............ 17

ለ. የትጥቅ ትግል ............ 21

III. አሳሳቢ በሆኑት ውስጣዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ላይ ያለን አቋም ......

1. የመሬት ጉዳይ ............ 22

2. የከተማ ቤትና የገጠር ቤቶች ጉዳይ ...... 30

3. የኤርትራ ጉዳይ ............ 32

4. የኢትዮጵያ ኃይሎች ............ 34

5. ኢምፔሪያሊዝምና ስለ ሦስተኛው ዓለም ... 36

6. የውጭ ጉዳይ አመራር ............ 37

ብቻ የተፈጠረ ተደምሮቱዋ ቶሎ ሰይጥን፡—

(ሀ) ጥቂት የትግራይ ሕዝብ ከሰማንያ (80) ዓመት በላይ ትግል ባደረገ ጀብሁ ፍሬ —

(ለ) ተራማጅ ትግሉ ከ1962 ዓ.ም ጀምሮ ፀንሶት የነበረውን አንጋፋ ልጅ ነው።

** ስለ ጊዜ ትክክለኛ የትግራይን ታሪክ ለማወቅ "የትግራይ ታሪክ፣ መሬትና ሕዝቦቿ" በሚል ርዕስ ተ.ሐ.ህ.ት. ያዘጋጀውን መጽሐፍ መመልከቱ ይጠቅማል። —

—ሃዐ—



# መግቢያ

የመደብ ብዝበዛና ብሔራዊ ጭቆና በሰፈነበት ሥርዓት ንቁና ተራማጅ የሆኑ ሁሉ ከተጨቋኙ ሰፊ ሕዝብ ጋር ሆነው ለተጨቋኙ ሕዝብ ጥቅም ሲሉ ብሔራዊና ሕብረተሰባዊ ዓላማዎችን ያዘለ መሠረታዊ ለውጥ (አብዮት) የማካሄድ ቅዱስ ኃላፊነት አለባቸው።

የተጨቆኑት ሰራተኞችና ድሀ ገበሬዎች የሚያሳትፍ ኢኮኖሚያዊ ብዝበዛና ፖለቲካዊ ጭቆና ደርሶባቸው በተለያዩ ዘዴ የተቃወሙ ትግል በሚያደርጉበት በአሁኑ ጊዜ ለሰፊው ሕዝብ የሚቆረቆሩ ተራማጆች ትግሉን የሚመሩትና አብዮ-ታዊ መስመሩን የሚያስይዝ ታሪካዊ ግዴታ አለባቸው። በዚህም አቋም እንቅስቃሴያቸውም በአብዮታዊ ወታደራዊ መንግሥት በመካሄድ ላይ ያለው ጦርነት ለውጥ ምክንያት ሊደርስ የቻለው የገበ-ሬዎችና ጭቆና ሊጠፋ የሚችለው በተደጋጋሚ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ብቻ ነው። ትሁን እንጂ የተደጋጋሚ አብዮታዊ እንቅስቃሴ በማካሄድ በማርክሲዝም-ሌኒኒዝም በሆነ ርዕዮተ-ዓለም በማስተባበር አስተባብሮ የሚመራ አብዮታዊ ድርጅት ያስፈልጋል።

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የምርት ግንኙነት

በጥብቅ ያወግዛል።

5. ከዲሞክራሲና ከህብረተሰብአዊ ዕድገት በመታገል ላይ ለሚገኙት የላቲን አሜሪካና የእስያ ህዝቦች ያልተቆጠበ የሞራል ድጋፉን ይሰጣል።

ፋሽሽታዊ ደርግ ይውደም!

ኢምፔርያሊዝም ይንኮታኮት!

ድምቀት ለዓለም ተራማጅ ሃይሎች!

የትግራይ ህዝብ ትግል ያሸንፋል!!

—x—

## [illegible] ቅኑዕ ብሄራዊ ቃልሲ መደባዊ ቃልሲ እዩ።

## Genuine National Struggle is in ESSENCE Class Struggle

ኣብ ጭቁናት ብሄራት ካብ ዝርከብ ህዝቢ ብዝኸፍአ ዝሳቀዩ ኣቶም ዝምዝመዙ ርጉፅ- በከላትን ሓረስቶትን ከምኡ'ውን ካልኦት ብሸቕሊ ዝናበሩን እዮም። እዚ ድማ ብሄራዊ ጭቆና መደባዊ ጭቆና ምዃኑ ስለዘርኢና--- ኣንጻር ብሄራዊ ጭቆና ዝገበር ቃልሲ'ውን ኣንጻር መደባዊ ጭቆናን ኣንጻር መድሓርሓርትን ጠላማትን ተወላዶ ዓዲ ብሄር ዝገበር ቃልሲ ምዃኑ ዘይጠራጠር ሓቂ እዩ።

Among the people of the oppressed nationalities, those who actually suffer are mainly the oppressed and exploited classes, the workers, peasants and other labouring classes. From this we can see that national oppression is in reality class oppression, and that the struggle against national oppression is in reality a struggle against class oppression; and often simultineously a struggle against the reactionaries and traitors of one's own nationality.

ተ.ሓ.ህ.ት.



ብሄራዊ ማዕርነትን መሉእ ናፅነትን ንምርካብ ውፁዕ ህዝቢ
ትግራይ ብተ.ሓ.ሀ.ት. ተሰሪዑ ዘሃብሎ <u>ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ ቃልሲ</u>
ብምክያድ ነቲ ንስካሕኒሕዎ ዘሎ ብሄራዊ ጭቆና ሃፀይታትን መዘናት
ክሩኹ ሮግዑ ክድምስስ ኢዩ።።ከምኡውን መደብ መዝመዝትን
ስርዓት ምዝመዛን ክበሩኑ ንምብርዳድ ኣቲ ቃልሱ ናብ
<u>ሶሻልዊ ቃልሲ</u> ክሰጋገር ናይ ቀርነት ክቲ ክንምጎግም'ዩ።።

In order to achieve national equality and total emancipation, the oppressed people of Tigray nationality, under the guidance of T.P.L.F. will resolutely carry out <u>national democratic revolution</u>, put an end to the national oppression of the imperialists and overthrow the rule of their lackeys; they will then carry through the <u>Socialist revolution</u> and destroy all the exploiting classes and systems.

T.P.L.F.

—xxxoxxxoxxx—